## የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በሽያጭ ወደ ግል ይዞታ ለማዛወር እና የጋራ ልማት ፍላጎት ለማቅረብ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

**የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር- 002/2019 እና 003JI / 2019**

I. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ቀጥሎ የተመለከቱት ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ባለቤት ነው፡፡

II. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 445/2011 በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሰውን ድርጅቶች ለመምራትና ለማስፋፋት ፈቃደኛ ለሆኑና አቅም ላላቸው ባለሃብቶች **በሽያጭ የጨረታ ቁጥር 002/2019 እና** የጋራ ልማት ፍላጎት ማቅረብያ **የጨረታ ቁጥር 003JI / 2019** ለማስተላለፍ ይፈልጋል፡

III. **<u>የሽያጭ ጨረታ ቁጥር- 002/2019</u>**

1. ቢ.ኤም ኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ አ/ማ (48.67% የአክስዮን ድርሻ)……….አ.አ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በጨረታ ሰነድ ውስጥ በተጠቀሰው መስረት ማቅረብ አለባቸው፡፡

IV. **<u>የጋራ ልማት ፍላጎት ለማቅረብ የወጣ ጨረታ ቁጥር - 003JI/2019</u>**

2. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሰውን ድርጅት ለመምራትና ለማስፋፋት ፈቃደኛ ለሆኑና አቅም ላላቸው ባለሃብቶች የቀንጥቻ ሲትየም-ታንታለም ማዕድንን በጋራ ለማልማት ይፈልጋል፡፡

2.1 አመልካቾች ቢያንስ ለአምስት (5) አመታት በተመሳሳይ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው የሰሩ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸው መሆን አለባቸው፤

2.2 ተጫራቾች የቴክኒካል፤የአመራር ብቃት ፤አለም አቀፍ የገበያ ትስስርና የፋይናንስ አቅም ያላቸው መሆን አለበት፤

2.3 አመልካቾች የድርጅታቸውን ስም፣ ተጠሪ ባለቤት፤አድራሻ፣ ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ፣ አመታዊ ገቢና ሌሎች መረጃዎችን መግለጽ ይኖርባቸዋል፤

2.4 ተጫራቾች በግል ወይም በጋራ ኮንሰርትየም መስረተው ፕሮፖዛል ማቅረብ ይችላሉ፡፡

V. **ለሁለቱም ጨረታዎች፡-**

- ተጫራቾች በዚህ ጨረታ አፈጻጸም የተዘጋጁትን የጨረታ ሠነዶች ገርጂ በሚገኘው ውሃ ሥራ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ህንጻ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 204 በመቅረብ ለእያንዳንዱ የጨረታ ሠነድ ተመላሽ የማይደረግ

ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) ወይም የዚህን ተመጣጣኝ የሆነ በአሜሪካን ዶላር በመክፈል ሰኔ 07 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሠዓት መውሰድ ይችላሉ።

- ተጫራቾች የጨረታ ፕሮፖዛላቸውን ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ፣ የተጫረቱበትን ድርጅት ስምና የጨረታ ቁጥሩን በመጥቀስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ እስከ ጳጉሜ 01 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 9:00 ሰዓት ድረስ ማስገባት አለባቸው።
- ጨረታዎቹ ጳጉሜ 01 ቀን 2011 ዓ.ም.. ከቀኑ በ9:15 ሰዓት በ2ኛ ፎቅ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
- ተጫራቾች ለአንድ ድርጅት ወይም ከአንድ ድርጅት በላይ ለመግዛት መወዳደር ይችላሉ።
- ተጫራቾች ፕሮፖዛል የሚያቀርቡበት ቀን ዓ.ም ከቀኑ በ9:00 ሲሆን ከዚህ ዘግይቶ የመጣ ፕሮፖዛል ተቀባይነት የለውም።
- ኤጀንሲው ሁለቱንም ጨረታዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
- ጨረታው ወይም የጋራ ልማት ፍላጎት ማመልከቻው የሚቀርበው በሚከተለው አድራሻ ይሆናል።

**የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ**

**ስልክ፡-** 011 8 69 37 29/0118693781

**ፖ.ሣ.ቁ.** 11835

**ገርጂ በቀድሞው ኢምፔሪያል ሆቴል ፊት ለፊት ባለው ውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ህንጻ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር** 204

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**በጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር** 002/2019 **ወይም የጋራ ልማት ፍላጎት ማመልከቻ የጨረታ ቁጥር** 003JI/2019 **መሠረት ለ**_______________ **ድርጅት የቀረበ የጨረታ ፕሮፖዛል በማለት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።**

**የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ**